# እሬሳው ይወጣል

በሰፈሩት ቁና ፣ መሰፈር አልቀረ
እሰይ የምስራች ፣ መቀነስ ጀመረ
የመሃይም መንጋን ፣ እየገፈተረ
አሳዳጅ ተሳዶ ፣ አሳሪው ታሰረ
ዘራፊና ገዳይ ፣ ቂሊንጦ ታጎረ
ባገርና በህዝብ ፣ መቆመሩ ቀረ
የጫካው አገዛዝ ፣ ሞተ ተቀበረ ።

በቁምጣ የገባው ፣ የደደቢት አውሬ
ብስል የለባቸው ፣ ጋንታ ሙሉ ጥሬ
እንኳን ያጎፈረው ፣ ተብተው መምሬ
ተደምመን ነበር ፣ ግር ያለ ፣ ለወሬ
እንዲህ ሊፍረከረክ ፣ አጋሰስ ጉማሬ ።

እንደሰው ተከብሮ ፣ ሰርቶ የማይበላ
እከኩን በስርቆት ፣ መስሎት የሚከላ
አጋሰስ ይመስል ፣ ቀን ከሌት ሲበላ
ከወዳጅ ከዘመድ ፣ ሲናከስ ሲጣላ
ወገኑን በችጋር ፣ በርሃብ ሲቆላ
ቅሌትና ውርደት ፣ አመጣችው አዝላ
ቂሊንጦ ይግባና ፣ አፈር ደቼ ይብላ ።

የነ ሁሉ ብርቁ ፣ ያሰለቸ ጆሮ
በየመሸታው ቤት ፣ ጢምቢራቸው ዞሮ
እንደፌንጣ መዝለል ፣ ሃብዚ ነበር ፣ ድሮ
ጥጋባቸው መክኖ ፣ ቅስማቸው ተሰብሮ
ዕብሪት እንዳልነፋው ፣ አንገት አቀርቅሮ
ሃጎስም ተሸኘ ፣ ወደማከክ ኑሮ ፣
ተመስገን ፈጣሪ ፣ ዜማው ተቀይሮ
ከጫንቃችን ወርደው ፣ ተኩላና ቀበሮ
እንኳንስ የሰው ልጅ ፣ አረፈች ከበሮ
ከመነረት ዳነች ፣ አበሳዋን ቆጥሮ ።

ሽበጡን አጥልቆ ፣ ቁምጣና ዲሪቶ
ፊደል ያልቆጠረ ፣ "ሀ"ን አያውቅ ለይቶ
ቅማሉን አራግፎ ፣ አዲሳባ ገብቶ
የካቲካላ አባት ፣ አይጠረቃ በልቶ
በዝርፊያ በስርቆት ፣ አገርን አግምቶ
ይግባ እንጂ በተራው ፣ ከርቸሌ ተላጭቶ
ምንስ እድሜ አላቸው ፣ ሁሉም ጎብጧል ጃጅቶ
እሬሳው ይወጣል ፣ ሲሞት ተጎትቶ ።

ታዛቢው

November 15, 2018